በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የአፍሪካ ጤና ኮሌጅ ለገሀር ጊቢ ጉባዔ መዝሙር ክፍል የ 2018 ዓ.ም ለጉዞ መርሃግብር የተዘጋጁ መዝሙራት

<u>ማውጫ</u>

1. እግዚአብሔር ይመስገን.....2
2. ቸርነቱ.....2
3. ያከብርዋ ለሰንበት.....2
4. ኑ በእግዚአብሔር.....2
5. እውነተኛው ሰላም.....2
6. አድርገህልኛልና.....3
7. ቸርነትህ ነው.....3
8. አንደበቴም ያውጣ.....3
9. ሰዎች ደስ ይበለን.....4
10. እንደ እግዚአብሔር ያለ.....4
11. ከክርስቶስ ፍቅር.....4
12. በፍቅር ተሰቦ.....5
13. ንሴብሖ.....6
14. ለመስግንህ የኔ ጌታ.....6
15. ቸሩ ሆይ.....6
16. ናና አማኑኤል.....7
17. ቸርነተህ ብዙ.....7
18. ሰላም ለኪ.....7
19. ይቄድስዋ መላዕክት.....8
20. ሰላም ሰላም ለኪ.....8
21. ለማርያም.....8
22. ትህትናሽ ግሩም ነው.....9
23. የፍቅር እናት.....9
24. ክብረ ቅደሳን 9
25. ስምሽን ጠርቼ 10
26. ትምክተ ዘመድነ.....11
27. የብርሃን ደጅ ናት.....11
28. ደጅ ጠናሁ.....11
29. ሰአሊ ለነ ቅድስት 12
30. ውዳሴ ማርያም እጨኻለሁ.....12
31. ድንግል ሆይ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ...12
32. የኪዳን ጽላት.....12
33. ማህደረ መለኮት.....13
34. አማን በአማን.....13
35. አንቺ ቤተልሔም 13
36. የምስራች ደስ ይበለን.....13
37. ይኸው ተወለደ.....13
38. ምስለ ሚካኤል.....14
39. የስሙ ትርጓሜ.....14
40. ይበራል በክንፉ.....14
41. ብዙ ልጆች አሉት.....15
42. የራማው ልዑል.....15
43. ገባሬ መንክራት.....15
44. ገድሉ ታምራቱ.....16
45. አቡነ ሀብተ ማርያም.....16
46. ሰአሉ ለነ ቅዱሳን.....16
47. ቤተክርስቲያን አንተውም ከኖ.....17
48. በምድራዊ ህይወት.....17
49. ከደመና በታች.....17
50. ዝማሬ ዳዊትን.....18

1. እግዚአብሔር ይመስገን

እግዚአብሔር ይመስገን ይህችን ቀን ቀድሶ ለሰጠን/2×/

ከያለንበት ሰብስቦ(2×) ለዚህ ያደረሰን/4/

2. ቸርነቱ

ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ/2×/

ይክበር ይመስገን መድኃኔዓለም የዓለም ቤዛ/4×/

3. ያከብርዋ ለሰንበት

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት፤ (2)

ወኩሉ ፍጥረት አሳት ወአናብርት እለ ውስተ ደይን ያእርፉ ባቲ እስመ ባቲ ኣእረፈ እምኩሉ ግብሩ፤/2/

ትርጉም፦

ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃን በገነት/2/

ፍጥረታት በሙሉ አሳዎችና አንባሪዎች በመቃብር ያሉ ያከብሯታል
አምላክ በርሷ ስለ አረፈ ከስራው ሁሉ፤ /2/

4. ኑ በእግዚአብሔር

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን(2×)

ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን

ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገረን

ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን/2×/

የሰማዩን መንግስት ርስቱን ለሰጠን

ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታ ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል

ከዐለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ

ስምህን ላመስግነው ከጠዋት እስከ ማታ

በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛበት

ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት

ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት

በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም

ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም

ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን

እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ

በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ

የኢያቄም ስእለቱ የሐና እምነት

ለምኚልን ለእኛ ኪዳነ ምሕረት

5. እውነተኛው ሰላም

እውነተኛ ሰላም ያለው ከቤትህ ነው

እርዳኝ አልናወጽ እለምንሃለሁ /2/

ኃጢያቴን ሳስበው ልቤ ይጨነቃል

ካንተ መለየቴ ነፍሴን አድክሟታል

ወዳንተ መልሰኝ እኔ እመለሳለው

እውነተኛው ሰላም ያለው ከቤትህ ነው

በቅዳሴ ፀሎት ዘወትር እንዳልተጋሁ

በአደባባይ ቆሜ ስምህን እንዳልጠራሁ

ተሰነካክዬ ወድቄአለሁና

እርዳኝ አማኑኤል በሐይማኖት ልጽና

ዓይኔም እንባ ያምንጭ ያልቅስ ስለ ኃጢያቴ

የንሰሐ ትሁን ቀሪዋ ህይወቴ

በመዳኔ ስዓት በዛሬዋ እለት

ፍቅርህን አስቤ መጣው ካንተ ቤት

ጌታ ሆይ ጸጸቴን እንባዬን ተቀበል

አባትህ ነኝ በለኝ እኔም ልጅህ ነኝ ልበል

ዘይት ሳላዘጋጅ ድንገት መጥተህብኝ

በርህን በመዝጋት ከደጅ አታስቀረኝ

6. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነተህ አመሰግንሃለሁ እልል/2/

ለዓለመ ዓለም አማኑኤል እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም/2/

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ

የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ

ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ

ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ

ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ

እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ

ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ

ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ

የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ

በቀንም በሌሊትም ሁሌ ለሚያበራ

መንክር ለባሕርይህ ዕጹብ ለአንተ ሥራ

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል

ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል

ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና

ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

7. ቸርነትህ ነው

ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከዛሬ

ላመስግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ/2/

መከሊቴንም ቀብሬ ባሳዝንህ

መብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ

በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ

ብፍቅር ጎብኝተህ ከሞት አውጣኝ

ከቤትህ እርቄ መኾ ጠገብኩኝ

በረሐብ በእርዛት ተቸገርኩኝ

አምናለሁ አምላኬ እንድትምረኝ

ለይቅርታ መጣሁ ይቅር በለኝ

አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ

ባንተ ቸርነት ግን እመካለሁ

የከበደው ሸክሜ ይቀለኛል

ይቅርታ ለባርያህ ይደርሰኛል

በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር

ስራህን ለትውልድ ለመመስከር

እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ

አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ

በሰው እጅ መመካት አቁሚያለሁ

እረዳቴ አንተ ነህ አውቄያለሁ

አንተ ከጠበከኝ በህይወቴ

ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ

የኔን ሰራ ተወው ተግባሬንም

የመስቀሉን ነገር መርሳቴንም

አዚሜን አንሰተህ አንተን ልይህ

እየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

8. አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ

የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ

በገባዖን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ

ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ

ከኃጢያት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ

የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ

የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኛጋ

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ

ከቅዱሳን ጋር ስዘምር አብሬ

እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትሰቅብኝ

ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም

ለጣኦት እንድሰግድ ነገስታት ቢያውጁም

ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም

ፅናት ይሆነኛል ጌታ መድሃኔዓለም

9. ሰዎች ደስ ይበለን

ሰዎች ደስ ይበለን በአምላካችን

ከኃጢአት ባርነት ነፃ ላወጣን

ተነሱ እናመስግን ውለታው ብዙ ነው

ምን ይከፈለዋል ተመስገን ብቻ ነው

በኃጢአት በሽታ ወድቄ ሳለሁኝ

መድሃኒት ክርስቶስ ከውድቀቴ አነሳኝ

ስጦታው ብዙ ነው ለኔ የሰጠኝ

ተመስገን ብቻ ነው አምላክ ላንተ ያለኝ

እንደ በርጠሜዎስ እውር የነበርኩኝ

ዛሬ ግን በአምላኬ ድህነት አገኘሁኝ

ህጉ ለመንገዴ ብርሐን ሆኖኛል

የእርሱ ስለሆንኩኝ ሠላምን ሰጥቶኛል

በድንቅ አጠራርህ በፍቅር የጠራኽኝ

ከአጋንንት እሥራት ነፃ ያወጣኽኝ

አልፋና ኦሜጋ ዘላለም የምትኖር

ኤልሻዳይ የሆንከው አማኑኤል ተመስገን

የዕዳ ደብዳቤዬን ጌታዬ ቀደደው

የማዳኑን ሥራ በአይኔ አይቻለው

ቸርነቱ አያልቅም ድንቅ የሆነ ጌታ

ስሙን እናመሰግን እንዘምር በእልልታ

10. እንደ እግዚአብሔር ያለ

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና

እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና/2/

ባህር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ

ፈርዖን ወደቀ አልሠራም ትምክህቱ

ደካሞች ጸንተው ተራመዱ

ሀይለኞቹም ይኸው ተዋረዱ

የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው

ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው

ሀይለኞችም ቢበረታቱብን

እንፀናለን በእርሱ ተደግፈን

የተወረወረው የጠላታችን ጦር

ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚያብሔር

ለስላሴ ይድረስ ምስጋናችን

ተሸነፈ አዳኝ ጠላታችን

ባህር ላይ ሲራመድ ሞገስ አለው እሱ

በግርማው ሲነሳ ፀጥ ይላል ነፋሱ

የድንግል ልጅ እኛ ምናመልከው

ከሀሊ ነው የለም የሚሳነው

11. ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው/2/

መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/4/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/

እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/4/

ሳይነጋ ተነስተን እንግባ በጠዋት/2/

በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት/4/

የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው/2/

ግቡ ነጹህ ውኃ መሠረቱ ደም ነው/4/

ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/4/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/

ይኸው እዚህ አለ የማኑኤል ቤት/4/

12. በፍቅር ተሰቦ

በፍቅር ተሰቦ ወረደ ለኛ ሲል

የፍቅሩን ፍፃሜ ገለፀ በመስቀል

ለኛ ያላረገዉ ከቶ ምን አለና

አፋችን ዝም አይበል እናቅርብ ምስጋና

ደስ ይበለን ሰማያትን ቀዶ

" ታላቁ አባታችን

" የዘመናት ንጉስ

" እየሱስ ጌታችን

" የኤፍራታዉ ህፃን

" በዳዊት ከተማ

" ተወልዶ ማዳኑን

" ምስራች ተሰማ

እንዳንተ ያለ በሀጥያት ዉስጥ ወድቀን

" ስንኖር ተጎሳቁለን

" አምላክ የኔ ጌታ

" ከሞት ዉስጥ አዳንከን

" ዝናዉንም አዉሩ

" ለአህዛብ ሁሉ

" እንደ እግዚአብሔር ያለ

" ማንም የለም በሉ

ደስ ይበለን ወረደ ወደምድር

" ሰላሙን ሊሰጠን

" ሰላም ለእናንተ ይሁን

" ብሎ ሊሰብክልን

" በመስቀል ተሰቅሎ

" እኛን የተቤዠን

" ከሲኦል እስራት

" በፍቅሩ የፈታን

ሃሌ ሉያ ምስጋና በሰማይ

" ምስጋና በምድር

" ሁሉን ቻይ ለሆነዉ

" ለቸሩ እግዚአብሔር

" ሃሌ ሉያ ለእርሱ

" ለነፍሳችን ጌታ

" ዝማሬን አናቅርብ

" ከጠዋት እስከ ማታ

13. ንሴብሐ

ንሴብሐ /2/ ለእግዚአብሔር /2/

ስቡሐ ዘተሰብሐ /4 /

እናመሰግነው /2/ እግዚአብሔርን /2/

ምስጉን ነው የተመሰገነ /4/

ባህሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ

በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ

ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን

ህይወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል መከራም ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ እንደጠጣነው

ይህን ታላቅ አምላክ ኑ እናመስግነው

ሰዎች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል

ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል ፈተናው ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

14. ለመስግንህ የኔ ጌታ

ላመስግንህ የኔ ጌታ ላመስግንህ

ልቀኝልህ የኔ ጌታ ልቀኝልህ

ህይወቴ ነው ዝማሬዬ ትሩፋቴ

የሰጠኸኝ እንዳከብርህ አንተ አባቴ)(2)

ከኔ ሆነህ የምሰጥህ ባይኖረኝም

ከሰጠኸኝ የአንተን መስጠት አይከብኝም

ጥበቤ ነህ የምስጋና መሰረቴ

ዝማሬዬን ያፈሰስከው በህይወቴ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

ባዶ እኮ ነኝ የኔ ጌታ ምን ልቅዳልህ

በእጇ ላይ አንዳች የለኝ የምሰጥህ

ላንተ ክብር የሚመጥን ህይወት የለኝ

ዝማሬዬን በቸርነት ተቀበለኝ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

ከምድር ላይ ከአፈር ስትፈጥረኝ

ከምስጋና የተለየ ምን ስራ አለኝ

ቀንና ሌት በመቅደስህ እቆማለሁ

አምላኬሆይ ሳወድስህ እኖራለሁ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

እዝራ ስጠኝ የከበረ መሰንቆህን

ዳዊት ስጠኝ የሚፈውስ በገናህን

መዝሙር ቅኔ ተምሪያለሁ ከአባቶቼ

እዘምራለሁ ባንተ ፍቅር ተመርቼ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

15. ቸሩ ሆይ

ቸሩ ሆይ ቸሩ ሆይ ናና

ቸሩ ሆይ አማኑኤል ናና

የእሥራኤል መና ቸሩ ሆይ ናና

ቸሩ ሆይ መድኃኒዓለም ናና

ቸሩ ሆይ - - - ለዓይነ ስውር መሪ

ቸሩ ሆይ - - - ምርኩዝ መመኪያ ነህ

ቸሩ ሆይ - - - አንተን የሚመስል

ቸሩ ሆይ - - - ምንም ነገር የለም

ቸሩ ሆይ - - - ምሕረትና ፍቅርህ

ቸሩ ሆይ - - - ወሰን ወደር የለው

ቸሩ ሆይ - - - ሳንወድህ ወደኸን

ቸሩ ሆይ - - - ፈልገህ ጠራኸን

ቸሩ ሆይ - - - ሰምተህ እዳልሰማህ

ቸሩ ሆይ - - - አይተህ እንዳላየህ

ቸሩ ሆይ - - - ሁሉን ታልፈዋለህ

ቸሩ ሆይ - - - ምድራዊ አባት ነህ

ቸሩ ሆይ - - - አማኑኤል ጌታ

ቸሩ ሆይ - - - ቸሩ ፈጣሪያችን

ቸሩ ሆይ - - -ውለታህ ብዙ ነው

ቸሩ ሆይ - - - ለእኛ የዋልክልን

ቸሩ ሆይ - - - በከብቶች ማደሪያ

ቸሩ ሆይ - - - በዚያች ትንሽ ግርግም

ቸሩ ሆይ - - - ተወልዶ አዳነን

ቸሩ ሆይ - - - ጌታ መድኃኒዓለም

ቸሩ ሆይ - - - እልል በሉ ሰዎች

ቸሩ ሆይ - - - አንድ ላይ ዘመሩ

ቸሩ ሆይ - - - ስብሐት ለእግዚአብሔር

ቸሩ ሆይ - - - በአርያም በሉ

16. ናና አማኑኤል ና መድኃኒቴ

ጽድቅህን አልብሰኝ ይቅር መራቆቴ /2/

ናና አማኑኤል ና መድኀኒቴ

ፍቅርህን አልብሰኝ ይቅር መራቆቴ /2/

የምሕረት አባት አማኑኤል

የቸርነት ጌታ ''

ፊትህ የተመላ ''

ሁሌ በይቅርታ ''

ካለው ፍቅር በላይ ''

አባት ለአንድ ልጁ ''

አምላክ ይወደናል ''

አይጥለንም ከእጁ ''

መድኃኒቴ ልበል አማኑኤል

ድኛለው በሞትህ ''

ቁስሌ ተፈውሷል ''

በቁስልህ በሞትህ ''

ስሸጥህ አቀፍከኝ ''

ስወጋህ አይኔ በራ ''

በፍቅርህ አወጣኸኝ ''

ከዚያ ከመከራ ''

አንተ ከኔ ጋር ነህ አማኑኤል

አዎ ከኔ ጋራ ''

ድል አርገህልኛል ''

የጭንቄን ተራራ ''

በጉባኤ መሀል ''

አፌ አንተን አወጀ ''

የከበረ ደምህ ''

ነፍሴን ስለዋጀ ''

የድንግሏ ፍሬ አማኑኤል

የበላቴናዋ ''

የቤቴ ምሰሶ ''

የነፍሴ ቤዛዋ ''

መሠረቴ አንተ ነህ ''

ያሳደገኝ እጅህ ''

አተወኝም አንተ ''

ስለሆንኩኝ ልጅህ ''

17. ቸርነትህ ብዙ

ቸርነትህ ብዙ ምሕረትህ ብዙ
በጉዟችን እርዳን ጠባብ ነው መንገዱ
ድንቅ ነው አምላክ ሆይ ፍቅርህ ለእኛ
ድንቅ ነዉ ለእኛ አንተ ነህ መልካም እረኛ

አስራኤል ወደቀ እስራኤል ተነሳ/2/
መንገዱ አልቀናውም አምላኩን ቢረሳ/2/
የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔርን ይዞ 2/
ምን እንዳተረፈ አውቀታል በጉዞ/2/
አዝ
መንገዱ አይታክትም ጎዳናዉ የቀና/2/
እግዚአብሔር በፊትም ከኋላሞ አለና/2/
እርሱ በሌለበት ቢመችም መንገዱ/2/
አቅጣጫው ወደ ሞት አይቀርም መውሰዱ/2/
አዝ
በመንገዱ ዝለን ወድቀን መች ቀርተናል/2/
የያዕቆብ አምላክ ደግፎ አንስቶናል/2/
እግዚአብሔር ሲጠራን በቀደመው መንገድ/2/
ጉዞአችን ወዴት ነው በሞት ለመወሰድ/2/
አዝ
አምላክ ሆይ ፍቅርህን በልባችን ሳለው/2/
እስከሞት በመስቀል የወደደን ማነው/2/
በበረሃዉ ጽናት ሲጸናብን ርህቡ/2/
በረከት ሞላኸን ተረፈልን ምግቡ/2/

18. ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቁዐኪ
እምአርዌ ነዐዊ ተማህጸነ ብኪ/2/

በእንተ ሐና እምኪ ወኢያቄም አቡኪ ማሕበረነ ዮም ድንግል
ባርኪ/2/

ትርጉም፡- ሰላም ለአንቺ ይሁን እያልን እናታችን

ማርያም ሆይ እንሰግድልሻለን እንማልድሻለን ስለ

እናትሽ ስለ ቅድስት ሀና ብለሽ ስለ አባትሽ ስለ

ቅዱስ ኢያቄም ብለሽ ድንግል ሆይ ማህበራችንን
ባርኪልን።

19. ይዌድስዋ መላእክት

ይዌድስዋ መላእክት /2/ ለማርያም/2/

በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ በሓኪ

ማርያም ሀዳስዩ ጣዕዋ/2/

ትርጉም፡- በመጋረጃ ውስጥ መላዕክት ማርያምን

ያመሰግኗታል አዲሲቱ ጥጃ ማርያም እንዴት

ዋልሽ /እንዴት አደርሽ/ ይሏታል።

20. ሰላም ሰላም ለኪ

ሰላም(2) ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ(2)

የሕይወት መሠረት..... ሰላም ለኪ

የፍጥረት አለኝታ .....ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

ሁኝልን መከታ..... ሰላም ለኪ

በላዔ ሰብ ዳነ .....ሰላም ለኪ

ብዙ ነፍስ አጥፍቶ .....ሰላም ለኪ

ያንቺን ስም ለጠራ .....ሰላም ለኪ

ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ .....ሰላም ለኪ

ተማጽነንብሻል .....ሰላም ለኪ

ባማላጅነትሽ..... ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

አማልጅን ከልጅሽ..... ሰላም ለኪ

እኛም ብንከተል .....ሰላም ለኪ

በጎ ምግባርን .....ሰላም ለኪ

በሰላም በጤና .....ሰላም ለኪ

እንኖራለን .....ሰላም ለኪ

21. ለማርያም

ለማርያም/2/

እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/

የተዘጋች ደጅ - - - - - ለዘለዓለም

ህዝቅኤል ብሏል - - - - - ለዘለዓለም

ንፅሕት ናት በእውነት - - - ለዘለዓለም

በፍጹም ድንግል - - - - - ለዘለዓለም

አብነት አድርገን - - - - - ለዘለዓለም

እኛም እርሱን - - - - - ለዘለዓለም

በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን/2/

የዋህይት ርግብ - - - - - ለዘለዓለም

ሰላም አብሳሪ - - - - - ለዘለዓለም

ለጨለማ ሕይወቴ - - - - - ለዘለዓለም

ብርሃንን አብሪ - - - - - ለዘለዓለም

እማጸንሻለሁ - - - - - ለዘለዓለም

ድንግል ለነፍሴ - - - - - ለዘለዓለም

አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ/2/

እጅግ የበዛ ነው - - - - - ለዘለዓለም

ያለኝ ፍቅር - - - - - ለዘለዓለም

አይወሰንም - - - - - ለዘለዓለም

አይነገርም - - - - - ለዘለዓለም

በእርሷ ደስ ይለኛል - - - - - ለዘለዓለም

ሐሴት አደርጋለሁ - - - - - ለዘለዓለም

ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ/2/

ነይ ነይ ስላት - - - - - ለዘለዓለም

ቀንና ሌሊት - - - - - ለዘለዓለም

አትለየኝም - - - - - ለዘለዓለም

ለእኔስ ቅርቤናት - - - - - ለዘለዓለም

እፁብ እፁብ ብለው - - - - - ለዘለዓለም

አመሰገኗት - - - - - ለዘለዓለም

ክብሯን ሊገልፁት ቢያጥራቸው ቃላት /2/

22. ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም /2/

እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም /2/

ንፅሕት ስለሆንሽ - - - -እመቤቴ እመቤቴ

እንከን የሌለብሽ- - - - እመቤቴ እመቤቴ

የፍጥረታት ጌታ - - - -እመቤቴ እመቤቴ

በአንቺ ያደረብሽ - - -- -እመቤቴ እመቤቴ

የድንግል መመረጥ - -እመቤቴ እመቤቴ

ዘናው አስገረመን- - - -እመቤቴ እመቤቴ

እሳቱን ታቀፈች - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

የማይቻለውን - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ምርኩዜ ልበልሽ- - - - - እመቤቴ እመቤቴ

ጥላ ከለላዬ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ጋሻዬ ነሽ አንቺ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ለእኔ መመኪያዬ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

በዓለም እንዳልጠፋ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ሕይወቴ መሮብኝ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

እንደ ወይን አጣፍጭው - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ማርያም ድረሽልኝ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

የምስራቅ ደጃፍ ነሽ - እመቤቴ እመቤቴ

የሁላችን ደስታ - - - -እመቤቴ እመቤቴ

እሙ ለፀሐየ ጽድቅ- - -እመቤቴ እመቤቴ

የሁሉ ጠበቃ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል የድል አክሊል- - እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል የጽድቅ ስራ- -- - እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል መሰላል ነሽ - - -እመቤቴ እመቤቴ

የተዋሕዶ ተስፋ - - - - -እመቤቴ እመቤቴ

23. የፍቅር እናት

የፍቅር እናት የሰላም /2/

ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ማርያም

በሕይወቴ ውስጥ በኑሮዬ

ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ

ተደላደለ ልቤ

አንቺ አለሽና ከአጠገቤ

ምኞቴም ይሰመር ድብቅ ህልሜ

ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ

የጌታዬ እናት ነሽ

ኃይሌን ያደርጋል ጸሎትሽ

እንዴት እቀራለሁ ከመንገዴ

አደራ እናቴ አስቢኝ

ለሚያስጨንቀኝ ጠላት

ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ

ትናንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ

የለም ለነገ የሚያስፈራኝ

ሜዳ ይሆናል ተራራ

ልጅሽ ስላለ ከእኔጋራ

24. ክብረ ቅደሳን

ክብረ ቅደሳን ይእቲ /2/ ክብረ ቅደሳን /2/

ሙዳዬ መና ግሩም /4/ ሙዳዬ መና /2/

የቅደሳኑ ክብር ነሽና

እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና

የወለድሽልን የህይወት መና

ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ

ፅንስ ያዘልላል ሠላምታ ድምፅሽ

እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል

ሳንዘምርልሽ መቼ ይይመሻል

የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ

ታላቁን ብርሀን አየንብሽ

አትጨልምም ህይወታችን

ልጅሽ ስላለ ፀሐያችን

ሰዓሊለነ ሰላም ለኪ

ተማህፀነ በኪዳነኪ

ንዒ ርግብዬ ምስለ ወልድኪ

ሰማይ ወምድር ያወድሱኪ

25. ስምሽን ጠርቼ

ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ

የምጽናናበት ስምሽ ነውና

ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና

ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር

ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር

ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ

የዓለሙን መድኅን ወለድሽልኝ

ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ

በአሕዛብ ሀገር ስኖር ተሸጨ

ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ

ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ

ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ

አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ

ምን አቀርባለው ብዬ ስቸገር

ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር

ያሰብኩት አሳብ ደመና ሆኖ

ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ

ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም

በእመአምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም

እናት አባቴ ባያስታውሱኝ

ይህቺ ዓለም ንቃ ገፍታ ብተወኝ

አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ

ዐውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ

ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ

መከራ አብዝቶ ቢያሰቃየኝ

አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና

ውለታሽ ድንግል አለብኝና

ከፋዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ

አንቺን መውደዴን አያስተውኝ

በአሕዛብ መሐል ስምሽን ስጠራ

መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ

ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ

መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ

አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና

ውለታሽ ድንግል አለብኝና

26. ትምክተ ዘመድነ

ትምክተ ዘመድነ (2)ማርያም እምነ

ማርያም ትምክተ ዘመድነ

የድኅነታችን አርማ የነፃነታችን

የህይወት መሠረት ነሽ ድንግል እናታችን

አንቺ ለኛ ዘርን ባያስቀር

እንደ ጥንቱ እንደ ሰዶ ምድር

ሁላችን በጠፋን ነበር

የአብርሀም ድንኳን ነሽ አምላክ ያደረብሽ

የጌዲዮን ፀምር ለይቶ ያከበረሽ

የኛ ቤዛ በጉ የተያዘብሽ

የዋህ ርግብ ከአበው ስር የተገኘሽ

እፀሳቤት የህይወት ሀረግ ነሽ

አምላክ ከሰማይ ሆኖ ይቺን አለም ሲቃኝ

ንጽህት ቅድስት ሆነሽ ማርያም አንቺን ቢያገኝ

ትህትናሽን ህይወትሽን ወዶ

ቃል ሰው ሆነ ከሰማያት ወርዶ

አከበረሽ በፍፁም ተዋህዶ

የመዳናችን ምክንያት የሰው ልጆች ሰላም

ከኃጢያት ከመርገም የዳነብሽ አለም

አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን

በሲኦል ውስጥ ተግዘን የኖርን

ድንግል ባንቺ ነፃነት አገኘን

27. የብርሃን ደጅ ናት

የብርሃን ደጅ ናት ድንግል እናታችን

ከሰማይ እያበራች ደስ አለው ልባችን

ፍቅርሽን ሰላምሽን ድህነት ይሁንን ኧ ኧ

ፍጥረት በሙሉ(2)ፊትሽ ይወድቃሉ

ፀጋሽ ይድረሰን(2)ይሰጠን እያሉ

የእኔ ልብ ምን ፅድቅ አለው አንቺ ለማስተናገድ

የሀጥያት ጎተራ ነው የተሞላው በስሥት

ኧረ እንዴት(2) ድንግል ትኑርበት ኧ ኧ

አትፀየፍም የእኔ ልብ ታሳናዳዋለች

ስለሀጥያቴ የእኔ እናት ምልጃ ታቀርባለች

ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት

ህሊናቸው ይመለስ እንፀልይ ለዚህ ጥፋት

አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትመጣው ኧ ኧ

እሷን ስንመልስ ጌታ ነውን የምናስቀይመው

28. ደጅ ጠናሁ

ደጅ ጠናሁ ቆይቼ ኪዳነምህረትን

ተፅናናሁኝ ረሳሁ ሀዘኔን

የአምላክ እናት እመቤታችን

ሞገስ ሁኚኝ ቀሪው ዘመኔን /2/

የመከራው ዘመን አለፈ እንደዋዛ

አንቺን ተጠግቼ የአለሟ ቤዛ

የልጅሽ ቸርነት ያንቺ ደግነት

ባሪያሽን ሰወረኝ ካስጨናቂ ሞት

እናቴ ስምሽን ስጠራ

አለፈ ያሁሉ መከራ

እንባዬ ከፊትሽ ፈሰሰ

እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ

ሰላም ለኪ

ልቤ ባንቺ ፀና ከፍከፍም አለ

በጠላቶቼም ላይ አፌ ተናገረ

በማዳንሽ ስራ ባርያሽ ደስ ብሎኛል!

የሀያሉን ቀስት ልጅሽ ሰብሮልኛል

እናቴ ስምሽን ስጠራ

አለፈ ያሁሉ መከራ

እንባዬ ከፊትሽ ፈሰሰ

እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ

ሰላም ለኪ

እጄ ባዶ ሲሆን ወዳጆቼም ሸሹ

በመርገም ምክራቸው ሊለያዩኝ ሲሹ

እሱ የሰጠኝን እሱ ወሰደ አልኳቸው

እመቤቴ አለችኝ ብዬ አሳፈርኳቸው

እናቴ ስምሽን ስጠራ

አለፈ ያሁሉ መከራ

እንባዬ ከፊትሽ ፈሰሰ

እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ

ሰላም ለኪ

በአውደ ምህረቱ ሆኜ ስጠራት

ዘንበል ብላ አየችኝ ኪዳነ ምህረት

ሃሳብሽን ምንም የለ የሚመስለው

እረፍት ያገኘሁት እናቴ ባንቺ ነው

እናቴ ስምሽን ስጠራ

አለፈ ያሁሉ መከራ

እንባዬ ከፊትሽ ፈሰሰ

እምዬ ባንቺ ነው የታበሰ

ሰላም ለኪ

29. ሰአሊ ለነ ቅድስት

ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን /2/

እንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን

ለምኝልን እመቤታችን/2/

ተስፋ አንቺ ነሽና ለፍጥረተ ዓለም

እየተመኩብሽ እስከ ዘለዓለም

ኃጢአታቸው ተደመሰሰላቸው

በአንቺ ፀሎት ዳነች ህይወታቸው/2/

ስምሽም ስልጡን ነው በእግዚአብሄር መንበር

ቃልኪዳን ገባልሽ ልጆችሽን ሊምር

በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ

ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ/2/

ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት

ነፍሳችን ስትደክም ሲከባት ኃጢአት

መንገድ ጠፍቶን ግራ ሲገባን

ብርሃናችን ነይ እናታችን/2/

የልባችን ሐዘን እጅግ ከብዶብናል

ከበለሱ በታች በፍርሃት

ወድቀናል እንደ ኤልሳቤጥ እንደ ዘመድሽ

ደስ አሰኝን ይሰማን ድምፅሽ/2/

30. ውዳሴ ማርያም እጮኻለሁ

ውዳሴ ማርያም እጮኻለሁ

ድንግል እናቴን እጣራለሁ

እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ

ወድሰኒ ልጇ በይኝ

ውዳሴ ማርያም____ በሰርክ ጸሎት ላይ

ውዳሴ ማርያም____ ዜማ ስናደርስ

ውዳሴ ማርያም____ ድንግል ትመጣለች

ውዳሴ ማርያም____ በቤተ መቅደስ

ውዳሴ ማርያም____ የብርሐን ምንጣፍ

ውዳሴ ማርያም____ ከፊቷ ተነጥፏል

ውዳሴ ማርያም____ ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ

ውዳሴ ማርያም____ ያመሰግናታል

ውዳሴ ማርያም____ አባ ሕርያቆስ

ውዳሴ ማርያም____ ምስጋና ያደርሳል

ውዳሴ ማርያም____ የቅዳሴው ዜማ

ውዳሴ ማርያም____ ልብን ይመስጣል

ውዳሴ ማርያም____ በጎ ነገር ልቤ

ውዳሴ ማርያም____ አወጣ እያለ

ውዳሴ ማርያም____ ዳዊት በገናውን

ውዳሴ ማርያም____ እየደረደረ

ውዳሴ ማርያም____ የንጽሕናችን

ውዳሴ ማርያም____ መሰረት ነሽና

ውዳሴ ማርያም____ አንቺን ለማመስገን

ውዳሴ ማርያም____ ልቦናዬ ይብራ

ውዳሴ ማርያም____ ተፈስሒ ድንግል

ውዳሴ ማርያም____ ኦ ቤተልሔም

ውዳሴ ማርያም____ ካንቺ ተወለደ

ውዳሴ ማርያም____ መድኃኒዓለም

ውዳሴ ማርያም____ ቅዱሳኑ ሁሉ

ውዳሴ ማርያም____ ዙሪያሽን ከበዋል

ውዳሴ ማርያም____ ቅዱስ ጊዮርጊስም

ውዳሴ ማርያም____ ንዒ ድንግል ይላል

ውዳሴ ማርያም____ በወርቅ ዙፋን ላይ

ውዳሴ ማርያም____ ተቀምጠሽ ሳይሽ

ውዳሴ ማርያም____ ልቤ ተሰወረ

ውዳሴ ማርያም____ ድንግል በግርማሽ

32. ድንግል ሆይ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ

ድንግል ሆይ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆናል

እመቤቴ ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆናል

ደካማ ነኝ እኔ ምግባር ይጎለኛል /2/

በሥጋዊ ሳይሆን በመንፈስ ዓይኖቼ

ለማየት እሻለሁ ከልቤ ጓጉቼ

ሥራዬ የከፋ መሆኑን አውቃለሁ

ስምሽንም መጥራት እጅግ እፈራለሁ

ክብርሽ የበዛ ነው ቤዛዊተ ኩሉ

ምህረት ታሰጫለሽ ላመነብሽ ሁሉ

በአንቺ የተመካ ምንም አያገኘው

የገሀነም እሳት ሲያልም አይበላው

የልዑል ማደሪያ የሲና እፀ ጸጦስ

አንቺን ላመስግንሽ ከህመሜ እንድፈወስ

ፍቀጅልኝ ድንግል ካንቺ ጋር እንድኖር

ልጅሽን ማልጅልኝ እንዲያበቃኝ ለክብር

ምንም ምግባር የለኝ ያላንቺ አናቴ

እመካብሻለሁ እስከለተ ሞቴ

የምስኪኖች አጽናኝ የችግሬ ደራሽ

የልቤ ማረፊያ ክብሬ ሞገሴ ነሽ

የጌታዬ እናት ድንግል እመበቴ

ተጠብቃ ትኑር ባንቺ ዘንድ ህይወቴ

የትሕትና ምንጭ የፍቅር ውቅያኖስ

ጠጥቸ ልርካብሽ ድንግል እንድፈወስ

33. የኪዳን ጽላት

የኪዳን ጽላት የተሰወረ መና ያለብሽ ደብተራ ድንኳን አንቺ ነሽ(2)

ይሄውም መና የተባለዉ(2)በድንግል ማርያም ያደረዉ
የእግዚአብሔር አብ ልጁ ነዉ(2)

33. ማህደረ መለኮት

ማህደረ መለኮት(2)

ማርያም እመ ብዙሐን(2)

34. አማን በአማን

አማን በአማን(2)መንክር(2)

መንክር ስብሐተ ልደቱ(2)

35.አንቺ ቤተልሔም

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት

ባንቺ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/2/

አዝ

የአዳምን ክብር ሲሻ ቤተልሔም

ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም

ጌታ ተወለደ ቤተልሔም

ከድንግል ማርያም ቤተልሔም

አዝ

ሕፃኑና እናቱን ቤተልሔም

በበረት አግኝተው ቤተልሔም

የምሥራቅ ነገሥታት ቤተልሔም

እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም

አዝ

ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም

አሸበሸቡለት ቤተልሔም

ስብሐት ለእግዚአብሔር ቤተልሔም

ብለው ዘመሩለት ቤተልሔም

36.የምስራች ደስ ይበለን

የምስራች ደስ ይበለን (2)

የዓለም መድኃኒት ተወለደልን

አዝ

ኢየሱስ የዓለም ቤዛ(2)

የዓለም ቤዛ (3) ለኛ ተወለደልን

አዝ

ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ (2)

ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ (2)

አዝ

ሰብዐ ሰገል እንደታዘዙት (2)

በኮከብ ተመርተው ህፃኑን አገኙት (2)

አዝ

ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው (2)

ወርቅ እጣን ከርቤውን በረከቱን ሰጥተው (2)

37. ይኸው ተወለደ

ይኸው ተወለደ የዓለም መድኀኒት /3/

እሰይ ተወለደ የዓለም መድኀኒት/3/

አዝ

ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ ሁሉ (3)

አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ (3)

አዝ

ሰብአ ሰገል መጡ እጅ መንሻ ይዘው /3/

ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤውን ገበሩለት ሰግደው /3/

አዝ

ምእመናን እንሂድ ከልደቱ ቤት/3/

ውነው ሆኗልና ማርና ወተት/3/

አዝ

ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ /3/

የእስራኤል ንጉሥ ተወልዷል እያሉ /3/

አዝ

በሶርያ ታየ ፈጣሪ እንደ እንግዳ/3/

ብሥራተ ልደቱን ለሁሉ ሊያስረዳ/3/

38. ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ማርያም/2/ንዒ ድንግል ንዒ/2/ ድንግል ምስለ ሚካኤል/2/ ኧኸ

ትርጉም፡- መልካሚቱ ማርያም ድንግል ከሚካኤል እና ከገብርኤል ጋር ነይ።።

38. የስሙ ትርጓሜ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው

የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው

እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጅው

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው

ከጉድጓድ ተጥሎ ፍጹም ከሚያስፈራው

ከተራቡት አናብስት ዳንኤል ያዳንከው

እናንም ተራዳን ቸል አትበለን

ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን

የክፉ ሰው ሥራው ክፉ ሃሳብ ነውና

በቅንነት መንገድ ከቶ አይሂድምና

የሞቱን ደብዳቤ ለባሕራን ሲሰጠው

ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው

ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ

ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምስጋናን ጀምሬ

ጸጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር

የሚካኤል ኣምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

39. ይበራል በክንፉ

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው

የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው

ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከኔ ጋር ነው (2)

አዝ

ከፊቴ ቀደመ ደመናን ዘርግቶ

እንዳልደናቀፍ ጉድባዎቼን ሞልቶ

ዛሬ ላለሁበት ብሩቱ ጉልበት ሆነኝ

ሰው ለመባል በቃሁ ሚካኤል ደገፈኝ

አዝ.

በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ

አለሁ እስከዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ

የህይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከርሱ ጋራ

ተፅፏል በልቤ የሚካኤል ስራ

አዝ

በዙሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሰሶውን

ፅድቅ እየመገበ ኣሳደገኝ ልጁን

የአምላኬን ምስጋና ዘውትር እያስጠናኝ

እርሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ

አዝ

ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር

ይስማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር

ይወስደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ

ታላቁት በረከት በውስጤ አፈሰሰ

አዝ

ሴኬምን እንዳላይ ከንፎቹን ጋረደ

መራኝ ወደ ህይወት መዳኔን ወደደ

የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ

በፀጋው ቃል ቃኘኝ በበረከት ሞልቶ።

40. ብዙ ልጆች አሉት

ብዙ ልጆች አሉት ለስሙ ምስክር

በዙሪያው ያሉትን አብቅቷል ለክብር

ስለፍፁም ምልጃው ለኔግን ይለያል

መላኩ ሚካኤል ስለው ደስ ይለኛል

ከመላዕክት ክብሩ ከፍ ከፍ ብሎ

በአምላኬ ተሾመ ዘንዶውንም ጥሎ

አሳዳጊዬነው ሆኖ እናት አባቴ

ሚካኤል ባለበት ይሸሻል ጠላቴ

ከሚታየው ሁሉ ልቤ ከሚፈራው

ካላየሁት ነገር ጠላት ከሰወረው

ያድነኛል ፈጥኖ በመንገዴ ወቶ

ሚካኤል ሀያሉ ክንፎቹን ዘርግቶ

በባህራን ታሪክ በነተላፊኖስ

በአፎምያ መትረፍ በነ ዱራታኦስ

በነብዩ ዳንኤል መኙ ይፈጸምና

የሚካኤል ስራ ይቀጥላል ገና

በጉዞ የረዳቹ በባህር በየብሱ

ፈጥኖ ደርሶላቹ እንባን ስታፈሱ

ስለታችሁ ሰምሯል ቁሙ ለዝማሬ

በሚካኤል ምልጃ የቆማችሁ ዛሬ

ክብር ለሚገባው ክብርን እንሰጣለን

ንጉሥ ለወደደው አንሰግድለታለን

እንኳን ለሚካኤል ለሚቆም ጌታ ፊት

ክብርን እንሰጥ የለ ለምድር ሹማምንት

41.የራማው ልዑል

የራማው ልዑል ገብርኤል/2/

ተመላለስ መሀላችን ስምህን ጠርተን ና ስንልህ/2/

ብርሃን ልብሱ እሳታዊው መልአክ

አንተ አማልደን ከመሐሪው አምላክ/2/

የምሥራች ነጋሪ ድንቅ ልደት አብሣሪ

የጽድቅ ፋና የድኅነት ጎዳና/2/

ላመኑብህ ለተማፀኑህ

ፈጥኖ ደራሽ አለኝታቸው ነህ/2/

የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል ከለላቸው

ከእሳት ነበልባል ያዳንካቸው/2/

ምስሶ ዓምዳችን መጠጊያችን

ቅዱስ ገብርኤል ጠባቂያችን/2/

42. ገባሬ መንክራት

ገባሬ መንክራት በገድሉ ያወቅነው

የእግሮቹ ትቢያ የአራዊት ስንቅ ነው

ገብረመንፈስ ቅዱስ የአምላክ ዓቃቤ ሕግ

የኢትዮጵያ ዋስ ነው ፈጥኖ የሚታደግ

ፀሐይ ፀሐይ ለምድራችን ፀሐይ

በገድሉ ያበራል እስከ ጥልቁ ከላይ

የመላእክት ወዳጅ(2)ገብረ ሕይወት ሰማይ

መብረቅ መብረቅ ሠረገላው መብረቅ

የቃል ኪዳኑ ወንዝ ቢጠጣ የማይደርቅ

የፍጥረቱ ደስታ(2)ገብረ ሕይወት ጻድቅ

ኮከብ ኮከብ ክብረ ገዳም ኮከብ

ዓለምን የሚያስንቅ መዓዛው የሚስብ

አልክ ሥሉስ ቅዱስ(2)ገብረ ሕይወት ኪሩብ

ስኒን(2)ቄና ልብሱ ስኒን

የነፍስን አዳራሽ በገድል የሚሸፍን

የሚነበብ መጽሐፍ(2)ገብረ ሕይወት ድርሳን

መቅረዝ(2)የማኅቶት መቅረዝ

ምድረ ከብድ ዝቋላን ያለመለመ ወንዝ

የዚጊቲው ፈዋሽ(2)ገብረ ሕይወት ምርኩዝ

43. ገድሉ ታምራቱ

ገድሉ ታምራቱ እጅግ ብዙ ነው

ጣዖትን አዋርዶ የተሸለመው

የተዋህዶ ኮከብ ተክለ ሐዋርያ

አባ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ

ዳግማዊ ዩሐንስ ጠፍር የታጠቀ

ፍፁም ባህታዊ ጠላት ያስጨነቀ

የፀጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ

በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ

ደካማ መስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት

ባለ ስድስት ክንፉ ተክልዬ የእኔ አባት

እርሱስ አንበሳ ነው ይናገር ደብረ አስቦ

ሌጊዮን ሲዋረድ እፍረት ተከናንቦ

ከካህናት መካከል ሀሩይ ነው ተክልዬ

መጣሁ ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ

ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት

ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት

የባረከው ውሃ የረገጥከው መሬት

ጥላህ ያረፈበት ሆኗል ፀበል እምነት

ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ

ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

44. አቡነ ሀብተ ማርያም

አቡነ ሀብተ ማርያም የዓለም ብርሃን ናቸው(2)

ይህው ለዘላለም ያበራል ስራቸው(2)

45. ሰአሉ ለነ ቅዱሳን

ሰአሉ ለነ ቅዱሳን መላእክት /2/

ሰአሉ ለነ ጻድቃን ሰማዕት

ሀበ አምላክ ምህረት ሰአሉ ለነ

ለምኑልን ቅዱሳን መላእክት /2/

ለምኑልን ጻድቃን ሰማዕታት

ወደ አምላክ ምህረት ለምኑልን/2/

አንተ የመረጥከውን ማን ይከሳል

ያጸደከውን ማን ይወቅሳል

ለሚገባው ክብርን መስጠት

ታሂልና በመጸሕፍት

ያከበርካቸው ባሪያዎችህን

እናከብራለን ቅዱሳንህን/2/

ጽኑ መዳንን እንዲይዙ የሚላኩ የሚታዘዙ

ሠርክ በፊትህ እየቆሙ

ጥዑም ቅዳሴን እያሰሙ

በምስጋናቸው የሚያከብሩህን

እናከብራለን መላእክትህን/2/

ጤዛ ልሰው ዳዋ ጥሰው

ዋእይ ቁሩንም ታግሰው

በየፍርክታው በየዱሩ

ሌጦ ለብሰው እየዞሩ

በስራታቸው ያከበሩህን

እናከብራለን ዳድቃንህን/2/

እንደሚታረድ በጐች ሆነው

አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው

ስለሰምህ እየተጣሉ

ከአንበሳ ጋር እየታገሉ

በተጋድሏቸው ያከበሩህን

እናከብራለን ሰማታትን /2/

ከህያው ቃልህ እየጠቀሱ

መናፍቃንን ድል እየነሱ

በገዛ ደምህ የዋጀሀትን

ቤተክርስቲያንን የጠበቋትን

በሕይወታቸው ያስደሰቱህን

እናከብራለን ቅዱሳንህን/2/

46..ቤተክርስቲያን አንተውም ከቶ

ቤተክርስቲያንን አንተውም ከቶ

የሰጠንን አምላክ በደሙ መስርቶ

የሰጠንን ጌታ በመስቀሉ ሞቶ

የአምላካችንን ቤት አንተውም ከቶ

ሁሉንም በሁሉ በሚሞላው ጌታ

ሙሽራው የሆነ ቤቱ ተሰኝታ

በክብር በሞገስ በጸጋ ተሞልታ

ደምቃ ትኖራለች ለዓለም አብርታ/2/

ዲያብሎስ ቢጨርስ ቀስቶቹን በሙሉ

ወጥመድ ቢዘረጋ በጉዞአችን ሁሉ

እንሻገራለን የአምላክን ስም ጠርተን

አንዳች አይነካንም እርሱን ተጠግተን/2/

በስሙ መሰብሰብ በስሙ መስራት

ስለ ስሙ መኖር ለስሙ መሞት

ጠላት ዲያብሎስን ምን ባያስደስት

ይህ ነው ክርስትና ይኼ ነው ሕይወት/2/

ከትውልድ ለትውልድ የምናስረክበው

ለልጅ ልጅ አውርሰን ደስ የምንሰኘው

አይደል ብርና ወርቅ አይደል ሌላ ሀብት

ሃይማኖታችን ነው የእኛ ርስት ጉልት/2/

48. በምድራዊ ህይወት

በምድራዊ ህይወት(2) በፈተና ቦታ(2)

ማርያም ትጠብቀን እጆችዋን ዘርግታ(2)

49. ከደመና በታች

ከደመና በታች እንዳይቀር ጸሎቴ(2)

አሳርጊው ድንግል እመቤቴ አሳርገው ሚካኤል አባቴ(2)

50. ዝማሬ ዳዊትን

ዝማሬ ዳዊትን ተልዕኮ አርድዕትን ቅዳሴ መላእክትን(2)

የተቀበልክ አምላክ(4) የእኛንም ዝማሬ ተቀበል(2)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር